# ለውጭ ገበያ በሚቀርብ በከፊል የተዘጋጀ ቆዳና ሌጦ ላይ የተጣለውን ታክስ ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 217/2013

በቆዳና ቆዳ ውጤቶች ዘርፍ የተሠማሩ ኢንዱስትሪዎች ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡት ምርት ደረጃ ተሻሽሎ አገሪቱ ከዘርፉ የምታገኘው የውጭ ምንዛሪ ከፍ እንዲል ለማድረግ ለውጭ ገበያ በሚቀርብ በከፊል የተዘጋጀ ቆዳና ሌጦ ላይ ታክስ የተጣለ በመሆኑ፣

የታክሱ መጣኔ አነስተኛ በመሆኑ ምክንያት ከፍተኛ መጠን ያለው ቆዳና ሌጦ በከፊል በተዘጋጀ (በክረስት) ደረጃ ለውጭ ገበያ የሚላክ ሲሆን፣ ይህ ሁኔታ በአገር ውስጥ የጥሬ ቆዳና ሌጦ አቅርቦት እጥረት እንዲኖር በማድረግ ያስከተለውን የዋጋ ያለመረጋጋት ማስወገድ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

እሴትን ከመጨመር እና የሥራ ዕድልን ከመፍጠር አኳያ የጎላ አስተዋፅዖ የሚኖረውን የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ ልማት ለማስፋፋት ኢንቬስትመንት ለመሳብ የሚያስችልና አስተማማኝ ያለቀለት ቆዳ አቅርቦት መፍጠር በማስፈለጉ፣

በክረስት ደረጃ ለውጭ ገበያ እየቀረበ ያለው ቆዳና ሌጦ ተገቢውን ዋጋ እያገኘ ባለመሆኑ የእሴት ጭማሪ በሚያስገኙ የምርት ሂደቶች ውስጥ እንዲያልፍ በማድረግ ባለቀለት ቆዳ ወይም በቆዳ ውጤቶች መልክ ለውጭ ገበያ በማቅረብ አገሪቱ ከንዑስ ዘርፉ የምታገኘው የውጭ ምንዛሪ እንዲጨምር ማድረግ ተገቢ በመሆኑ፣

ከዚህ የሚከተለው መመሪያ ወጥቷል፡፡

## 1. አውጪው ባለሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ለውጭ ገበያ በሚቀርብ ጥሬ እና በከፊል የተዘጋጀ ቆዳና ሌጦ ላይ ታክስ ስለማስከፈል በሚደነግገው አዋጅ ቁጥር 567/2000 አንቀጽ 7 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## 2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ «ለውጭ ገበያ በሚቀርብ ጥሬ እና በከፊል የተዘጋጀ ቆዳና ሌጦ ላይ የተጣለውን ታክስ ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 217-2013» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 3. <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ መመሪያ ውስጥ

3.1 «ክረስት የበሬ ቆዳ» ማለት በክሮም ወይም በቬጂቴብል ወይም በክሮምና በቬጂቴብል ወይም በሌሎች የቆዳ ማልፊያ ኬሚካሎች ከለፉ በኋላ በዘይት የተጠመቀ፣ የተቀለመ ወይም ያልተቀለመ ሆኖ የደረቀና ለማጠናቀቅ የምርት ሂደት የተዘጋጀ የበሬ፣ የላም እና የሌሎች የቀንድ ከብቶች ቆዳ ነው፡፡

3.2 «ክረስት የበግ ሌጦ» ማለት በክሮም ወይም በቬጂቴብል ወይም በክሮምና በቬጂቴብል ወይም በሌሎች የቆዳ ማልፊያ ኬሚካሎች ከለፉ በኋላ በዘይት የተጠመቀ፣ የተቀለመ ወይም ያልተቀለመ ሆኖ የደረቀና ለማጠናቀቅ የምርት ሂደት የተዘጋጀ የበግ ሌጦ ነው፡፡

3.3 «ክረስት የፍየል ሌጦ» ማለት በክሮም ወይም በቬጂቴብል ወይም በክሮምና በቬጂቴብል ወይም በሌሎች የቆዳ ማልፊያ ኬሚካሎች ከለፉ በኋላ በዘይት የተጠመቀ፣ የተቀለመ ወይም ያልተቀለመ ሆኖ የደረቀና ለማጠናቀቅ የምርት ሂደት የተዘጋጀ የፍየል ሌጦ ነው፡፡

3.4 «ያለቀለት የበሬ ቆዳ» ማለት ከዚህ መመሪያ ጋር ተያይዞ በቀረበው ያለቀለት ቆዳ ኖርም ውስጥ በተዘረዘሩት የማጠናቀቂያ መንገዶች የተመረተ ሆኖ ለቆዳ ውጤቶች ማምረቻ እንዲውል የተዘጋጀ የበሬ፣ የላም ወይም የሌሎች ቀንድ ከብቶች ቆዳ ነው፡፡

3.5 «ያለቀለት የበግ ሌጦ» ማለት ከዚህ መመሪያ ጋር ተያይዞ በቀረበው ያለቀለት ቆዳ ኖርም ውሰጥ በተዘረዘሩት የማጠናቀቂያ መንገዶች የተመረተ ሆኖ ለቆዳ ውጤቶች ማምረቻ እንዲውል የተዘጋጀ የበግ ሌጦ ነው፡፡

3.6 «ያለቀለት የፍየል ሌጦ» ማለት ከዚህ መመሪያ ጋር ተያይዞ በቀረበው ያለቀለት ቆዳ ኖርም ውስጥ በተዘረዘሩት የማጠናቀቂያ መንገዶች የተመረተ ሆኖ ለቆዳ ውጤቶች ማምረቻ እንዲውል የተዘጋጀ የፍየል ሌጦ ነው፡፡

3.7 «ያለቀለት ቆዳ ኖርም» ማለት ያለቀለት ቆዳ ወይም ሌጦን ምንነት ለመወሰን የተዘጋጀ ሰነድ ሆኖ ለውጭ ገበያ የሚቀርበው ያለቀለት ቆዳ ማሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች የሚወሰንባቸውን ዝርዝር ጉዳዮች የያዘ ሰነድ ነው፡፡

3.8 «አዋጅ» ማለት ለውጭ ገበያ በሚቀርብ ጥሬ እና በከፊል የተዘጋጀ ቆዳና ሌጦ ላይ ታክስ ለማስከፈል የወጣው አዋጅ ቁጥር 567/2000 ነው::

3.9 በዚህ መመሪያ ጥቅም ላይ የዋሉ ሌሎች ቃላትና ሐረጐች በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ::

## 4. ማሻሻያ

ለውጭ ገበያ በሚቀርብ ጥሬ እና በከፊል የተዘጋጀ ቆዳና ሌጦ ላይ የሚከፈለው ታክስ እንደሚከተለው ተሻሽሏል::

ሀ) ጥሬ ቆዳና ሌጦ ከዋጋው 150%
ለ) ዌትብሎ የበሬ ቆዳ ከዋጋው 150%
ሐ) ፒክልድ የበግ ሌጦ ከዋጋው 150%
መ) ዌትብሉ የፍየል ሌጦ ከዋጋው 150%
ሠ) ክረስት የበሬ ቆዳ ከዋጋው 150%
ረ) ክረስት የበግ ሌጦ ከዋጋው 150%
ሰ) ክረስት የፍየል ሌጦ ከዋጋው 150%

## 5. ያለቀለት ቆዳ ኖርም

ማንኛውም የቆዳ አምራች ለውጭ ገበያ የሚያቀርባቸው ባለቀለት ደረጃ የተዘጋጁ ቆዳና ሌጦዎች ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተውን ያለቀለት ቆዳ ኖርም ያሟሉ መሆን ይኖርባቸዋል::

## 6. ለውጭ ገበያ የሚቀርብ ቆዳ ወይም ሌጦን በተመለከተ የሚፈለጉ መረጃዎች

ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት ቆዳና ሌጦን ወደውጭ አገር ሲልክ የሚከተሉትን መረጃዎች አሟልቶ ማቅረብ አለበት::

ሀ) የቆዳ ወይም የሌጦ ምድብ የበሬ ወይም የበግ ወይም የፍየል መሆኑን፣

ለ) ቆዳው ወይም ሌጦው የተመረተበት ዓላማ ለጫማ ሽፋን፣ ለአልባሳት፣ ለጓንት፣ ለገበር ወይም ለሌላ መሆኑን፣

ሐ) የቆዳው ወይም የሌጦው የውፍረት መጠን በሚሊ ሜትር፣

መ) የቆዳው ጥራት ደረጃ በምርጫ ውጤቱ መሠረት ከ1ኛ - 3ኛ፣ 4ኛ፣ 5ኛ፣ 6ኛ ወይም ውዳቂ ወይም A, B, C, D, E መሆኑን፣

ሠ) የቆዳው ወይም ሌጦው የቀለም ዓይነት ቀይ፣ አረንጓዴ፣ ጥቁር፣ ቡናማ፣ ግራጫ፣ ወዘተ መሆኑን፣

ረ) የቆዳው የሌጦው ብዛት በቁጥር ወይም በስፋት መጠኑን በካሬ ጫማ ወይም በካሬ ሜትር የሚያሳይ ሰነድ፣

ሰ) የቆዳው ወይም የሌጦው ነጠላ ዋጋ ወይም አጠቃላይ ዋጋ በውጭ ምንዛሪ እና በብር መሆኑን የሚገልፅ መረጃ፣

## 7. <u>አዋጁንና መመሪያውን የማስፈፀም ኃላፊነት</u>

1. የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

ሀ) ከአገር የሚወጡ ዕቃዎችን ለመፈተሽ፣ ለመመዝገብ፣ ለመቆጣጠር እና ታክስ ለማስከፈል በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ወደውጭ አገር የሚላኩ የቆዳና ሌጦ ምርቶችን የመፈተሽ፣ የመመዝገብ የመቆጣጠርና ታክስ የማስከፈል ተግባራትን ያከናውናል፡፡

ለ) ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት በአዋጁና በዚሁ መመሪያ መሠረት ቀረጥ ተከፍሎበት ወደውጭ አገር እንዲላክ የተወሰነን ምርት ቀረጥ ሳይከፍል ለመላክ ቢሞክር ወይም ቢልክ በጉምሩክ አዋጅ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ጉዳዩን የመመርመር፣ የመክሰስ፣ የማስቀጣት እንዲሁም ክስ የማንሳት ተግባራትን ይፈፅማል፡፡

2. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እንደአስፈላጊነቱ ያለቀለት ቆዳ ኖርምን እየከለሰ እንዲፀድቅ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ያቀርባል፡፡

3. የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት

ሀ) ከተቋቋመበት ዓላማ አኳያ ይህንን መመሪያ ለማስፈፀም የሚረዱ ማናቸውም ሙያዊና ቴክኒካዊ እገዛዎችን ያደርጋል፣

ለ) ኢንስቱትዩት ከማናቸውም ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ጥያቄ ሲቀርብለት ከዚህ መመሪያ ጋር ተያይዞ ከቀረበው ያለቀለት ቆዳ መስፈርት አንፃር ሲታዩ አጠራጣሪ ሆነው የተገኙ የቆዳና ሌጦ ምርቶችን መርምሮ የውሣኔ ሀሳብ ያቀርባል።

8. <u>ስለመሻር</u>

ለውጭ ገበያ በሚቀርብ የተዘጋጀ ቆዳ ላይ የተጣለውን ታክስ ለማሻሻል የወጣው መመሪያ ቁጥር 25/2001 ተሽሮ በዚህ መመሪያ ተተክቷል።

9. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ከታህሣሥ 1 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

*አዲስ አበባ ኅዳር 22 ቀን 2004 ዓ.ም*

*ሱፍያን አህመድ*
*የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት*
*ሚኒስትር*